በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia

ኢ ት ዮ ጵ ያ
ETHIOPIA

የአካባቢ፣የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
Environment, Forest and Climate change Commission

ቁጥር 11/14.1/4716/11
Ref.No.
ቀን 18/11/2011
Date

ለኢትዮጵያ የታሸገ ውሃና ለስላሳ መጠጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በፕላስቲክ ኮዳ የታሸገ ዉሃ መክደኛ ላይ የሚደረገውን ኔክ ስሊቭ (Neck Sleeve/Seal) መጠቀምን ስለመከልከል፤

መስሪያ ቤታችን በቁጥር 11/14.1/4165/11 በቀን 26/10/2011ዓ.ም ለማህበራችሁ በጻፈው ደብዳቤ በፕላስቲክ ኮዳ የታሸገ ውሃ መክደኛ ላይ የሚደረገውን ኔክ ስሊቭ መጠቀም ማስቀረት እንዲቻል አውንታዊ ምላሽ መስጠቱ ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ የታሸገ ውሃ ጥራት ደረጃን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት በግልባጭ በደረሰን ደብዳቤ፡-

ሀ/ የኢትዮጵያ የምግብ መድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በቀን 13 መጋቢት 2011 በቁጥር 02/12/29/911 በጻፈው ደብዳቤ ኔክ ስሊቭን በተመለከተ ደረጃ አለመኖሩን በመጥቀስ ኔክ ስሊቭ ከምርት ደህንነትና ጥራት ወይም ተጠቃሚው ሊያገኘው ከሚገባው መረጃ ጋር የተገናኘ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡

ለ/ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ለማህበሩ በቁጥር 4/2/1/45/11 በቀን 17 ሐምሌ 2011 በጻፈው ደብዳቤ ኔክ ስሊቭ (Neck Sleeve) ጸድቀው ስራ በሚገኙ የታሸገ ውሃ የኢትዮጵያ ደረጃዎች CES 99 (Bottled water) እና CES 151 (Mineral botteled water) ያልተካተተ መሆኑንን በመጥቀስ ከውሃ ጥራት ደረጃ ጋር ተያያዥነት የሌለው መሆኑንን አሳውቋል፡፡

በመሆኑም በሀገራችን ከዘርፉ የሚመነጨው የፕላስቲክ ቆሻሻ

1. በስብሶ ከአፈር ጋር የማይወኃድ፤ ለአፈርና ከርሰ ምድር ውሃ መበከል መንስኤ የሚሆን በመሆኑ፤
2. ከቆሻሻ ጋር የተጣለ ኔክ ስሊቭ አሰባሰቡ እንዲሁም ለመልሶ ዕውደት የሚያስፈልገው የሀይል ፍጆታ ሊያስገኝ ከሚችለው ፋይዳ ጋር የሚነጻጸር ባለመሆኑ፤

☎ 251-(0)11-170-40 60 ቴሌ ፋክስ TELE FAX: 251-(0)11-170-4158/45
251-(0)11-170-40 39
251-(0)11-170-40 11 ✉12760
አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia
Website: www.mefcc.gov.et

የአየር ንብረት ... ሪከርድና ማህደር
Environment, Forest & Climate Change Commission Record & Archive

አምራች ተቋማት በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/1995 አንቀጽ 3/3 መሰረት ብክለትን ወይም ሌላ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትል በሚችል የተግባር መስክ የተሰማራ ማንም ሰው የቆሻሻ መመንጨትን ለማስወገድ ወይም ወደ ተፈላጊው መጠን ለመቀነስ በተገቢ ቴክኖሎጂ መጠቀም ያለባቸው በመሆኑ ከሐምሌ 16 2011 ዓ.ም ጀምሮ የኔክ ስሊቨን መጠቀም እንዲቆም እያሳወቅን ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር የምናደርግ መሆኑንን እንገልጻለን፡፡

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን * Environment, Forest & Climate Change Commission *

ከሰላምታ ጋር

ፍሬነሽ መኩሪያ
ም/ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>

ለክቡር ኮሚሽነር

<u>የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን</u>

- ለየንግድ እና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስለጣን
- ለየምግብ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንደስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
- ለኬሚካል እና ግንባታ ግበዓት ልማት ኢንስቲትዩት
- ለየኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ

<u>አዲስ አበባ</u>